# አቶ እንዳልካቸው ይርጉ (ቺኪ)

እንዳልክ (ቺኪ) ብዙ በሳል ሰው ነበር። ቁም ነገሩና ጥንካሬው እጅግ የቀና የሚሰራውን፣ የሚያወራዉን፣ የሚጫወተውን፣ የሚያነበውን፣ የሚወደውን፣ የሚያከብረውን፣ የሚመክረውን፣ የሚቃወመውን፣ የሚደግፈውን፣ አሳምሮ የሚያውቅ ውድ ጓዳችን ጓደኛችንና መካሪያችን ነበር። ቺኪ ለሀገሩና ሕዝቡ ራዕይ ያለው ጠይቆና መርምሮ አውቆ ትግላችን ወዴት መሔድ እንዳለበት ወደኋላ ሳይልና ሳያወላውል አዘውትሮ የሚከራከርና የሚያሳምን ሁላችንንም በእኩል የሚመለከት ጠንካራ ግለሰብ ነበር። በርቱ ይል ነበር አዘውትሮ። የሕዝባችንን ብሶት መስማት ከቻልን መፍትሔውን ማፍለቅ ይቻላል። አሁንም መስዋዕትነት ከከፈልን ማደራጀት ማንቀሳቀስ ይቻላል። ሕዝባችንን ባላሰለስና ተግባራዊነት ባነገበ ትግል ከድህነት አዙሪት ማውጣት ይቻላል። ኢትዮጵያዊነትና ኢትዮጵያን ለዘለዓለም ማቆም ይቻላል ብሎ የሚያምን ነበር።

ቺኪ ለሀገሩ ኢትዮጵያና ለሕዝቡ ያለውን ፍቅር በተለያዩ የግጥም ስብስቦቹ ሲያንጎራጉርና ሲጽፍ ሕይወቱን የኖረ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጅ ነበር። በ2006 የታተመው “ልብ በሉ ሰዎች እና ኑ ብለዋችኋል” በሚለው አጫጭር የግጥም ስብስቦቹ፡ እምነትን፡ እውነትን፡ ፍቅርን፡ እያስተማረን ለሀገርና ሕዝብ ተቆርቋሪነቱንም ያስነብበናል። ኢትዮጵያ ሁለገብ ልጇን አጣች። ለጓደኞቹ አዛኝ፡ አሳቢ፡ አሰባሳቢ፡ መካሪና አስተማሪ የነበረው ቺኪ ዛሬ ትዝታውንና የማይነጥፉ ውብ ሥራዎቹን ጥሎልን አልፏል። ኢትዮጵያ አንድ ጠንካራ ተከራካሪዋንና ጠበቃዋን አጣች። እንጉርጉሮውንና ዝማሬውን ለሀገርና ሕዝብ እንዳደረገ፡ በጥፋጭ ብዕሩ እንዳስነበበ ያለፈ አኩሪ የዚያ ትውልድ ወገናችን ነው። ወንድም ቺኪ በደረሰበት ህመም ቢለየንም የተከበራችሁ ቤተሰቦቹ፡ በመጨረሻው የሕይወት ፈተና ወቅትም አብራችሁ ለነበራችሁ ለተከበራችሁ ጓዶቹና ጓደኞቹ ዓላማና ፅናቱ ሁሌም ይከተለን።



**እንዳልካቸው ይርጉ** 1952 - 2004 **እ.ኢ.አ**

“ኢትዮጵያ ቆራጥ ልጅዋን አጣች፡፤ እኛም ጓዳችንና ወንድማችንን አጣን። ህመም እየበረታበትና ድካም እየተጫጫነው ከቆመለት ዓላማ ሳያዛንፍና ትግሉን ሳይጠራጠር እስከ መጨረሻ እስትንፋሱ ድረስ ታግሎ ማለፉ በህይወት ላለነው ትልቅ የሞራል ጥንካሬን ይሰጠናል። በትግል ሳይሸነፍ በህመም ተሸነፈ። የወንድማችን ስሙና ታሪኩ በኢትዮጵያ የትግል ማኅደር ለዘላለም ይኖራል። ፅናት ለዘመዶቹና ጓዶቹ”።






# የአቶ እንዳልካቸው አጭር የሕይወት ታሪክ

አቶ እንዳልካቸው ይርጉ ከአባቱ ከአቶ ይርጉ አባይነህና ከእናቱ ከወ/ሮ ወሰኔ የሱፍ በወሎ ክፍለ ሀገር በደሴ ከተማ ታህሳስ 7 ቀን 1952 ዓ.ም. ተወለደ። ቤተሰቡ በሥራ ምክንያት ወደ አዲስ አበባ ሲዛወር አብሮ በመጓዝ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በቀድሞው ልዕልት ጽጌ በሻህ ት/ቤት አጠናቋል። በመቀጠልም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በተፈሪ መኮንን ት/ቤት ለተወሰኑ ዓመታት ተከታትሏል።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እየተከታተለ ባለበት ወቅት የ1966 የኢትዮጵያ አብዮት ይፈነዳል። በዚህ ግዜ ሁሉንም የኢትዮጵያ ልጆች በእኩልነት የሚያይና፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን የሚያስከብር ሕዝባዊ መንግስት አስፈላጊነት ሀገሪቱን በወጠራት ወቅት እንዳልክ ገና ወጣት ነበር። በወቅቱ የዕድሜው ለጋነት ሳያግደው በዚህ ትግል ለሀገሩና ለወገኑ የምከፍለው ድርሻ አለኝ በማለት ትምህርቱን ባማቋረጥ ወደ ትግሉ ጎራ ገባ።

በወቅቱ በአዲስ አበባ ከተማ የደርግን አፋኝ ሥርዓት ከሚታገሉ ጓዶቹ ጋር በመሆን በአዲስ አበባ ከተማ የሰላማዊ ሰልፍና የቅስቀሳ ሥራዎችን በማስተባበር ወሳኝ ሚና ተጫውቷል። በዚህ ወቅት በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢ.ሕ.አ.ፓ) ወጣት ክንፍ ተመልምሎ ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት በመክፈል የህዝብ ልጅ መሆኑን አረጋግጧል።

እንዳልክ በወቅቱ የሚያደርገው ትግል በመንግሥት በመታወቁና እርምጃ ሊወሰድበት የሚችልበት ሁኔታ በመፈጠሩ በ1969 ዓ.ም ወደ በረሀ ለመሄድ ወሰነ። በአሲምባ ተራሮች የትጥቅ ትግል የጀመረውን የኢ.ሕ.አ.ፓ ሠራዊት (ኢ.ሕ.አ.ሠ) ወደ ትግራይ በመጓዝ ተቀላቀለ።

በሠራዊቱ ይሰጥ የነበረውን የሽምቅ ውጊያ ሥልጠና አጠናቆ፣

"...ብረት አነሳሁ
ለትግል ተነሳሁ
ልጓዝ በድል ጐዳና
በተሰዉት ጓዶች ፋና ..."

የሚለውን መዝሙር በመዘመር መራራውን ትግል ተያያዘው።

እንዳልክ 1970 ዓ.ም. በትግል ሜዳ፣ በጥይት ተመቶ የግራ ክንፍ ሳንባው ቢጐዳም፣ ከአሲምባ ኤርትራ፣ ከኤርትራ ጐንደር፣ ወልቃይት፣ ፀለምት፣ በለሳ፣ አርማጭሆና የጭልጋ በረሃዎችን ሲያቋርጥ በአካሉም ሆነ በሞራሉ ድካም ሳይታይበት ጉዞዎቹን አጠናቋል።



1973 ዓ.ም. ለህክምና ወደ ሱዳን ከወጣ በኋላ ወደ አሜሪካ መጣ። ኢ.ሕ.አ.ፓ በሰሜን አሜሪካ ድርጅታዊ መዋቅሩን ዘርግቶ እንቅስቃሴ በጀመረበት ግዜ እንደገና ተቀላቅሎ በተለያዩ ኮሚቴዎች ኃላፊነትን ተቀብሎ አገልግሏል። በዚህ ወቅት ቤተሰብ ቢመሰርትም ፣ ሥራውን፣ ቤተሰቡንና ማህበራዊ ሕይወቱን አመጣጥኖ በመምራት ሁሉንም ኃላፊነቶቹን በአግባቡ ተወጥቷል።

እንዳልክ (ቺኪ) በሰሜን አሜሪካ በሎስ አንጀለስ ከተማ ቀደምት የነበረውን የሥነ ጽሁፍ ክበብ ለማቋቋም ከፍ ያለ አስተዋጽዎ አድርጓል።

ይኸን ክበብ ለማቋቋም አባላቶችን በተለያዩ ሁኔታዎች ወደ ክበቡ በመጋበዝ ፡ በማበረታታትና ፡ እራሱም፡ ግጥሞች በመፃፍ "ጧፍ" የተባለ የግጥም መድብል በተከታታይ ከአባላቱ ጋር በመሆን አሳትሟል። የዚህ ክበብ አባላት በተለያየ ምክንያት ቁጥራቸው ቢቀንስም ሌላ ተመሳሳይ ክበብ አቋቁሞ "ጠብታ" በሚል መድብል የአባላትን የግጥም ስብስቦች ለዕትመት እንዲበቃ ከሌሎች አባላት በተለየ ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ጥሯል። ይህ ክበብ በሎስ አንጀለስ ከተማ እስከዛሬ ድረስ ሥነጽሁፉን ተወዳጅ ለማድረግ አሁንም በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። በዚህ ግዜ ውስጥ ሦስት የ"ጠብታ" መድብሎችና በግሉም "ልብ በሉ ሰዎች እና ኑ ብለዋችኋል" በሚል ርዕስ አጫጭር የግጥም ስብስቦች ለአንባቢያን አበርክቷል።

ቺኪ (እንዳልክ) በስነጽሁፍ ብቻ ሳይወሰን በከተማው ውስጥ በአማርኛ የሚተላለፍ የሬድዮ ፕሮግራም ለማቋቋም ከጣሩት ሰዎች ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል። "ልሳነ ኢትዮጵያ" የተባለው ይህ ሬድዮ በሚያቀርበው ሳምንታዊ ዝግጅት የመኖሪያ ቤቱን ለፕሮግራም ዝግጅት በማዋል የዝግጅቱ አቀነባባሪና አቅራቢ በመሆንም ተሳትፏል።

እንዳልክ ቺኪ በስፖርት መስክም በካሊፎርኒያ ሎስ አንጀለስ (LA STAR)ና አበበ ቢቂላ ለሚባሉት ክለቦች እግር ኳስ ተጫውቷል። በሎስ አንጀለስ ከተማ የነበረው የኢትዮጵያ ማህበረሰብን ተቋም ለማቋቋም በተለያየ ግዜ የተደረጉ ጥረቶች ቢኖሩም፡ እንዳልክ ማዕከሉን ለመመስረት ያደረገው ጥረትና በአስተባባሪነት ያገለገለው ግልጋሎት አሁንም ይታወሳል።

እንዳልክ በ2006 ዓ.ም. መኖሪያውን አትላንታ ከተማ በማድረግ አዲስ ኑሮ ጀመረ። እንዳልክ የጥበብ ጥማቱን ለማስታገስ በማሰብ ወደ ሎሬት ክበብ በራሱ መሪነት ተቀላቅሏል። በዚህም ጥበብ አፍቃሪ ግብዣ ሳይጠብቅ ወደ ጥበብ የሚሄድ መሆኑን በተግባር አስመስክሯል። በዚህ ክበብ ውስጥ "ሥነጽሁፍ በሽታ ነው፡ ልተውህ ብለውም አይተወኝም" በሚለው አባባሉ ይታወሳል። እንዳልክ በወር አንድ ግዜ የሚደረገው የግጥም ጉባዔ ላይ ግጥሙን ቆሞ በማንበብ ገጣሚዎችን በማበረታታት፡ አባላትን በመጋበዝ፡ የጉባዔውን ቀንና ቦታ በማስተባበር በአጠቃላይ ሁሉንም በመሆን ይህ ቀረህ የማይባል አባልና የክበቡ መሪ ሆኖ አገልግሏል። በዚህ ክበብ አባላትን የግጥም መድብል እንዲያሳትሙ፡ የግጥም ጉባኤዎች ለህዝብ እንዲቀርቡ በአመራርም በተግባር በመሳተፍም ተወዳዳሪና ተተኪ የማይገኝለት ስራ አከናውኗል።

እንዳልክ ከማንም በላይ ከመንገድ ወጥቶ ሰውን ለመርዳት ንጹህ ልብ የታደለ ሰው አክባሪና ለጋስ ነበር። በተለያዩ ግዜያት በሰዎች ላይ ለሚደርሱ ችግሮች ቀድሞ ደራሽ፡ መጠለያ ላጡ ቤቱ ወስዶ የሚያስተናግድ፡ የተቸገሩ ሰዎች ከችግራቸው የሚወጡበትን ሁኔታ በማመቻቸት ያልተቆጠበ ጥረት የሚያደርግ ነበር ። እንዳልክ ለበርካታ ኢትዮጵያውያን ወደዚህ አገር መምጣትና መቋቋም ያልጣረው ጥረት ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም።

እንዳልክ በግል ህይወቱም እዚህ አገር ከመጣ በኋላ በሎስ አንጀለስ ኮሙኒቲ ኮሌጅ አሶሲየት ዲግሪ በአርት (Associate Degree in Arts) በማጠናቀቅ ከዚያም በተጨማሪ በMedical Coding ጥናት በማድረግ በCCS የብቃት ማረጋገጫውን አግኝቷል። አቶ እንዳልካቸው በAmerican Health Information Management Association (AHIMA) አባል በመሆን አገልግሏል። በሥራ ዓለምም በሎስ አንጀለስ ከአገለገለበት ውስጥ LA Metropolian Hospital, King Hospital, Gurdinia Community Hospital ሲጠቀሱ፡ ከዚያም በአትላንታ Piedmont Hospital, Peidmont Fayettevill Hospital, Rockdale Medical Center ለበርካታ ዓመታት በተማረበት ሙያ አገልግሏል።

እንዳልክ ከባለቤቱ ከማርታ ነጋሽ ጋር በ01/17/2001 (እ.ኤ.አ.) ጋብቻ መስርቶ በትዳር ይኖር ነበር። ትዳሩን አክባሪና ለትዳሩ ሟችና ልጆቹን አፍቃሪ የነበረው እንዳልክ፡ እውነት፡ እምነት እና ኦሪት የተባሉ የሦስት ሴት ልጆች አፍርቷል።

ለበረሀው ንዳድና ውሃ ጥም፡ ለኑሮ ውጣ ውረድ፡ በአጠቃላይ ለማንኛውም ችግር እጁን የማይሰጠው እንዳልክ በጥቂት ወራት ውስጥ በአደረበት ህመም ምክንያት የወትሮ አቅሙ ቢሸሸውም ከፍተኛ ሞራሉና ለሰው ተጨናቂነቱ፡ ትህትናውና፡ ተጫዋችነቱ እስከመጨረሻው የህይወቱ ጠርዝ ድረስ አብረውት ነበሩ። አብረውትም ወደ መቃብር ወረዱ።

እንዳልክ ባደረበት ህመም በህክምና ሲረዳ ከቆየ በኋላ፡ ርህሩሁ እንዳልክ፡ ለሰው ተጨናቂው እንዳልክ፡ የማይሸነፈው እንዳልክ፡ ተሸንፎ ግንቦት 6 ቀን 2004 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

የወንድማችን ቺኪ የሕይወት ታሪኩን የሚዳስስ ልዩ የክብርና የመታሰቢያ ዝግጅትና የቀብር ሥነ ሥርዓት ከታች በተገለጸው ቀንና ቦታ እንደሚካሄድ እየገለጽን ለበባለቤቱ፡ ለልጆቹ፣ ለወንድም እህቶቹ ለአባቱና ለመላው ቤተሰብ፣ ዘመድ አዝማድና የትግል ጓዶቹ እግዚአብሔር ብርታቱንና ጥናቱን ይስጣችሁ/ይስጠን እንላለን።





# ካልታተሙ የቺኪ ግጥሞች

## ኑዛዜ

ይቆፈራል መሬት፣ ይወጣል አፈር
ጉድጓድ ይበጅና፣ ይሆናል ቀብር
ደጉ ያገሬ ልጅ ቀና ገራገሩ
ጠላቴም ወዳጄም ሁሉ ሰው ከበሩ
ይተክዛል ያዝናል፣ እኔው በመሞቴ
የገባው ጊዜና፣ ይህ ሁሉ እንግልቴ
አገሬ ግን ገና፣ ደጋጉን አብቅላ
ሰውን በባህሉ፣ በወጉ አማምላ
ሬሣየን አትወሰድ፣ አትሆነኝም ለኔ
እዚሁ ቅበሩኝ፣ ከስደት ምናኔ።

## ከነ-እምነቴ ልቆይ

ምን አልባት ምን አልባት
        እንደው ለምናልባት
እንደማይሆን እያወቅሁት
        ያማረ አንድ ሰው
                በእምነቱ ያደረ
ከነፍስ ከሥጋው እየተሻከረ
እውነት ባለው ጉዞ ሲባክን የኖረ
አንድ ሰው ነበረ
                ነበረ፣ ነበረ
ይባል ይሆን እንደው ቢጠቅም ባይጠቅም
እባካችሁ ተዉኝ ልቆይ ከእነእምነቴ
ታቅፌው ልንፏቀቅ ከቀሪው ሕይወቴ።

የአቶ እንዳልካቸው ይርጉ (ቺኪ) የክብር ሥነ ሥርዓትና የቀብር ሥነ ሥርዓት

የአቶ እንዳልክ የክብር መታሰቢያ ሥነ ሥርዓት

ቀን፥ አርብ May 18, 2012
ሰዓት፥ 4:00 - 8:00 P.M. Eastern Time
አድራሻ፥ Horis A Ward Funeral Home
1355 Rockbridge Road
Stone Mountain, GA 30087

የአቶ እንዳልክ የቀብር ሥነ ሥርዓት

ቀን፥ ቅዳሜ May 19, 2012
ሰዓት፥ 10:00 A.M. Eastern Time
አድራሻ፥ Kidiste Mariam Ethiopia Orthodox Church
1152 Stone Mountain Lithonia Road
Stone Mountain, GA 30058

ከቤተ ክርስቲያን የፀሎት ሥነ ሥርዓት በኋላ የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ቦታና አድራሻ

Melwood Cemetery
5170 E Ponce De Leon Ave
Stone Mountain, DeKalb, GA 30083



